Amharic

ሰራ የልዎትም ወይ?

ሊሰሩበት የሚችሉ ብዙ
አቅሞች አልዎት ወይ?

የራስዎ ንግድ
ለመጀመር ይፈልጋሉን?

# ለመጀመር መዘጋጀት

የግል ንግድ ያላቸው ስደተኞችን መርዳት
ለስደተኞች የሚሆን የመጀመር መመርያ

REFUGEES INTO BUSINESS

Refugees into Business
© The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

**This booklet is for guidance only.**

This project is funded by the Phoenix Fund and the Small Business Service of the Department of Trade and Industry.

This booklet is also available in the following languages: Amharic, Arabic, Dari, Farsi, French, Pushto, Kurdish Sorani, Portuguese, Somali, Swahili, Tigrignia and Turkish.

Refugees into Business is a project managed by Refugee Enterprise Partnership, lead by the Refugee Council.

The Refugee Enterprise Partnership consists of the British Refugee Council, Refugee Action (RA), Refugee Women's Association, Social Enterprise London, the Prince's Trust, Community Action Network, and Education Action International.

With thanks to the Language and Literacy Unit+ (LLU+), London Southbank University, who has helped ensure the text is accessible to people who are at least at entry level 3 in their reading of English.

www.refugeesintobusiness.org.uk/translated_ten_steps

© The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

Supported by PHOENIX FUND

# ይዘታዎች

## ለመጀመር መዘጋጀት

ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት አስር እርምጃዎች የራስዎን ንግድ ለመጀመር እንዲዘጋጁ የሚረዱ ናቸው፤


1. ራስ መተማመንን ማሳደር 3
2. በህጋዊ መንገድ የንግድ ስራዎን መጀመር እንደሚችሉ አስቀድመው ማረጋገጥ 5
3. ሲቪ (CV) (ስለ እርስዎ የትምህርትና የስራ ልምድ መረጃ ታሪክ) ማዘጋጀት 8
4. እንግሊዘኛ ቋንቋ በደምብ ለመግባባት እንዲችሉ እርዳታ ማግኘት 11
5. ንግድ ስራ ስልጠና ማግኘት 14
6. ባሉበት አከባቢ ወይም በማህበረሰብ ያሉት የንግድ ድርጅቶች ውስጥ የበጎ ፍቃድ ስራ ለመስራት 16
7. ልጆችዎ የሚቆዩበት ቦታ ማዘጋጀት 18
8. የሚያስፈልግዎት ገንዘብ ማዘጋጀት 20
9. ከንግድ ስራ ባለሞያ ንግድ የመጀመር ድጋፍ ማግኘት 23
10. ሌሎች የእርዳታ ምንጮች 26

 © The Prince’s Trust and the Refugee Council 2006

# ደረጃ 1፡ ራስ መተማመንን ማሳደር

ባለፉት መቶዎች አመታት ብዙ ስደተኞችና ስፋሪዎች ወደ እንግሊዝ አገር በመግባት በእንግሊዝ አገር ቁጠባ ላይ ጥቅም አስገኝተዋል። አንዳንድ በስደተኞች የተጀመሩ የንግዶችና የንግድ ሀሳቦች ባሁኑ ጊዜ በአገሪቱ በየቀኑ ኑሮ ላይ ድርሻቸውን እያበረከቱ ናቸው።

**ለምሳሌ፡ የሚከተሉትን ያውቃሉን…?**

- → የአሳና ድንች ጥብስ የመመገብን ባህል ስደተኞች ይዘዉት የመጡ ነው። ጆሴፍ ማሊን የተባለ ከምስራቅ አውሮጳ የመጣ ስደተኛ በ1860 የመጀመርያ የአሳና ድንች ጥብስ የሚሸጥበት ሱቅ በምስራቃዊው የለንደን ጫፍ ላይ ከፈተ።
- → አቶ ዴልዋት የተባለ በፈረንሳይ አብዮት ጊዜ ወደ ሃል ከተማ ከ200 አመታት በፊት የገባ ስደተኛ የሂሳብ ስራ ድርጅት አቋቋመ። የልጅ ልጁ የሂሳብ ድርጅቱን በሃገሪቱ በአንደኛ ደረጃ ከሚጠቀሱት ድርጅቶች አደረገው። በአሁኑ ጊዜ Deloitte and Touche በሚል ስም የሚሰራ አለምቀፋዊ ዝና ያገኘ የሂሳብ ስራ ድርጅት ሆኗል።
- → አሌክ ኢሲጎኒስ የተባለ የቱርክ አገር ስደተኛ ከቤተሰቡ ጋር በ 1922 እንግሊዝ አገር ገባ። <ሞሪስ ማይንር> እና <ሚኒ> የተባሉትን የእንግሊዝ አገር መኪኖችን ለአለም ያስታዋወቀ የመኪና መሃንዲስ ነበር።

**Marks & Spencer**

ሚካኤል ማርክስ በ1859 ስሎኒም በተባለ ቦታ ሩስያ ውስጥ ተወለደ። ወጣት እያለ ስደተኛ ሆኖ እንግሊዝ አገር ገባ። ምንም አይነት የሙያ ችሎታ ስላልነበረውና በእንግሊዝኛ የመግባባት እጥረት ምክንያት ሊድስ ከተማ ውስጥ ባራን የተባለ ስደተኞችን ይቀጥር ከነበረ ድርጅት ጋር ስራ ጀመረ። ቆይቶም ከሚሰራው ስራ ገንዘብ አጠራቅሞ አንድ እቃ ደርድሮ የሚሸጥበት ቦታ ሊድስ ገበያ ተራ ውስጥ አቋቋመ። ከዚህ መሸጫ ቦታው አለፍ ብሎ በትልቁ የተጻፈ ፖስተር፡ <ዋጋ አትጠይቁ፡ የማንኛውም እቃ ዋጋው አንድ ሳንቲም ነው> ይላል። ከጥቂት አመታት በኋላ ማርክስ ተመሳሳይ የባለ አንድ ሳንቲም እቃ የሚሸጥባቸው መደርደሪያዎች ገበያ አደራሾች ውስጥ በዮርክሻየርና በላንካሻየር በየቦታው ከፈተ።

በ1894 ማርክስ ስራውን ለማስፋፋት የሚያግዘው አንድ የስራ ባልደረባ እንደሚያስፈልገው ወሰነ። በዚህም መሰረት አንድ ቶም ስፐንሰር የተባለ ሰው አብሮት መስራት ጀመረ። ስፐንሰር ሚካኤል ማርክስን ለተወሰነ ጊዜ ስራውን ይከታተለው ነበር። ለንግድ ስራው ግማሽ ባለቤትነት የተጠየቀው

300 ፓውንድም እንደ ጥሩ ኢንቨስትመንት/መዋእለ ንዋይ እንደሚቆጠር ተረዳ። ሁለቱም በተግባቡት መሰረት ስፐንሰር ቢሮውንና መጋዘኑን እንዲሁም ማርክስ ገበያውን ማስተዳደር እንዲቀጥል ወሰኑ። ከቶም ስፐንሰር ጋር አብረው መስራት ከጀመሩ በኋላ ማርክስ በማንቸስተር፣ በበርሚንግሃም፣ በሊቨርፑል፣ በሚድልስብሮ፣ በሼፊልድ፣ በብሪስቶል፣ በሃል፣ በሳዘርላንድና በካርዲፍ ሱቆች መክፈት ቻለ።

በ1897 የ Mark & Spencer የንግድ ግዛት በስልሳ ስድስት ቅርንጫፍ ሱቆች መስራት ጀመረ። በ 1903 Mark & Spencer እንደ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲቆም በዛው አመት መጨረሻ ቶም ስፐንሰር ሃብታም ሰው ሆኖ ከስራው በጥሮታ ወጣ። ሚካኤል ማርክስ ግን የንግድ ድርጅቱን እንግሊዝ አገር ውስጥ ታዋቂ ከሆኑት ድርጅቶች አንድ እስከማድረጉ ያበልጥ በማሳደግ ላይ እንደነበረ በ 31 ታህሳስ 1907 ከዚህ አለም በሞት ተለየ።

የንግድ ስራዎ ትልቅም ይሁን ትንሽ፣ ገበያ ውስጥ የእቃ መደርደርያም ይሁን የሂሳብ ስራ ድርጅት፣ የተዋጣለት ሊሆን ይችላል። ማንኛውም ስራ የመሞከር መብት አልዎት ጥሩ ከሰራልዎት ጥቅሙ ለእርስዎ ብቻ ሳይሆን በሰፊው ለህብረተሰቡም ጭምር ነው። ሆኖም ግን የራስዎን ንግድ ለማደራጀት በሚያስቡበት ጊዜ ያሉትን እንቅፋቶችንና መሰናክሎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብዎት። ስለሆነም ማንኛውም ሰው የራሱ ንግድ ሲጀምር አንድ አይነት ውጤት ስለማይኖረው ንግዱን ከመጀመርዎ በፊት በደንብ ሊያስቡበት ይገባል። ይህ መመርያ ለነዚህ ችግሮች መፍትሔና ቀጥሎ ያሉት የድጋፍ ምንጮችን ለማግኘት ይረዳዎታል፣

→ ጀማሪ ነጋዴዎችን ለማደራጀት ከሚረዱ ድርጅቶች
→ ጓደኞችዎን፣ ቤተሰብዎንና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ያሉት አባላትን በማማከር።

እነዚህን እርዳታዎች በሙሉ በመጠቀም የንግድ ስራዎን የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ይችላሉ።

| ማድረግ ያለብዎት ነገር | ማድረግ የሌለቦት ነገር |
|---|---|
| ይህን ማብራሪያ ካነበቡ በኋላ በተለያየ መልኩ ድርጅትዎን ለማቋቋም ሊረድዎት የሚችሉ የሰዎችና የድርጅቶች ዝርዝር ስሞች ያዘጋጁ። | እዚህ ስራ ውስጥ ብቻዎን እንደሆኑ እንዳይሰማዎት። ስራውን የተሳካ እንዲሆን የሚያደርጉ በተለያየ መልኩ ብዙ እርዳታ በአከባቢዎ ማግኘት ይችላሉ። |


© The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

# ደረጃ 2: በህጋዊ መንገድ የንግድ ስራዎን መጀመር እንደሚችሉ አስቀድመው ማረጋገጥ

ህጉ እንደሚለው የሚቀጥሉትን ነጥቦች ሟሟላት የሚችል ሰው የንግድ ስራ ማቋቋም ይችላል፡

→ እንግሊዝ አገር ውስጥ የመስራት ፍቃድ እንዲሁም የመኖሪያ/መግቢያ ፈቃድ ካልዎት፤ የመኖርያ ፈቃድ በተለያየ መልኩ ሊሰጥ ይችላል፡

## 1. የስደተኛነት ፈቃድ ደረጃ ከተሰጥዎት፡

i. ከነሓሴ 2005 በፊት የስደተኛነት ፈቃድ ደረጃ (refugee status) ከተሰጥዎት ላልተወሰነ ጊዜ የመኖርያ ፈቃድ (Indefinite Leave to Remain (ILR)) ይዘዋል ማለት ነው። እንግሊዝ አገር ውስጥም ያለ ጊዜ ገደብ እንዲቆዩ ያስችልዎታል።

ii. የስደተኛነት ፈቃድ ደረጃውን ከነሓሴ 2005 በኃላ ያገኙት ከሆነ ግን የመኖርያ ፈቃድዎ ግዚያዊ ሆኖ ለ 5 አመታት ያገለግላል። በየ 5 አመቱ ጉዳይዎ በድጋሚ ተጠንቶ ወደ አገርዎ ለመመለስ የሚያግድዎት ችግር እየቀጠለ መሆኑ ከታመነበት ላልተወሰነ ጊዜ የመኖርያ ፈቃድ (ILR) ተሰጥትዎት ቆይታዎ ይራዘምልዎታል። የመመለስ ችግር የልዎትም ከታባለ ግን ወደ አገርዎ ተመልሰው ይላካሉ።

## 2. ግዚያዊ የመግቢያ/መኖሪያ ፈቃድ ቀጥሎ ካሉት ምክንያቶች አንዱ መሰረት ሲሰጥዎት ይችላል፡

i. የሰብአዊነት ከለላ (Humanitarian Protection) (ከነሓሴ 2005 በፊት ከሆነ እስከ 3 አመት ድረስ ይሰጣል። ከነሓሴ 2005 በኃላ ግን እስከ 5 አመት ድረስ ይሰጣል። በዚህ ጊዜ መጨረሻ ጉዳይዎ በድጋሚ ይጠናል። ወደ አገርዎ ለመመለስ የሚያግድዎት ችግር እየቀጠለ መሆኑ ከታመነበት የቆይታዎ ጊዜ ይራዘምልዎታል ወይንም ላልተወሰነ ጊዜ የመኖርያ ፈቃድ (ILR) ይሰጥዎታል። የመመለስ ችግር የልዎትም ከታባለ ግን ወደ አገርዎ ተመልሰው ይላካሉ) ወይንም፡

ii. ጊዚያዊ ነጻ የመኖርያ ፈቃድ (Discretionary Leave to Remain) (ለ3 አመት ወይንም ከዛ ላነሰ ጊዜ ይሰጣል። ከነሓሴ 2005 በኃላ ጉዳይዎ ከ 3 አመት በኃላ በድጋሚ እየተጠና ፈቃድዎ ሊራዘምልዎት

ወይንም ላይራዘምልዎት ይችላል። የተሰጥዎት ከለላ ከጥናቱ ኋበኋላ አስፈላጊ አይደለም ተብሎ ከታመነበት ወደ አገርዎ ተመልሰው ይላካሉ። እንግሊዝ አገር ውስጥ እስከ 6 አመት ለመኖር ከተፈቀደልዎት ላልተወሰነ ጊዜ የመኖርያ ፈቃድ (ILR) ይሰጥዎታል)።

ማስታወሻ፡ ህጋዊ የሆነ ጊዚያዊ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የመኖርያ ፈቃድ ተሰጥዎታል ሲባል (አብዛኛው ግዜ) ስራ መስራትና አንዳንድ መሰረታዊ የሆኑትን ነገሮች እገዛ መጠየቅ ተፈቅድዎሎታል ማለት ነው።

የመስራትና የመኖር ፈቃድ እንዳልዎት በምን ማወቅ ይችላሉ? የሚከተሉትን አጣርተው ይመልከቱ፡

→ የኢሚግረሽን ወረቀትዎን ወይንም
→ የአገር ውስጥ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት (Home Office) በሚሰጥዎት ህጋዊ ደብዳቤ የመስራትና የመኖር ፈቃድ እንደተሰጥዎት የሚጋልጽ ከሆነ።

በደንብ ይገልጻሉ። የፈቃድዎ ጊዜ ወደ ማብቂያው ከተቃረበ የንግድ ስራዎን ከመጀመርዎ በፊት ወረቀትዎን ያስተካክሉ። ይህን ለማድረግ፡

→ ቀጥለው ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ጋር በመገናኘት በዚህ ጉዳይ ሊረዳዎት ይችላሉ። ምን ማድረግ እንዳለብዎትም ይነግርዎታል።
→ ወደ አገር ውስጥ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ደብዳቤ ይጻፉ
→ ወደ አገር ውስጥ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ደውልው ወረቀትዎን ለማስተካከል የሚያስገቡት ማመልከቻ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ሊሰራ እንደሚችል ያረጋግጡ።

የመኖርያ ፈቃድ እንደተሰጥዎት በህጋዊ መንገድ ካሳወቅዎት በኃላ ስለ ንግድ ስራ የማቋቋም ዝግጅት ማሰብ ሊጀምሩ ይችላሉ።


© The Prince’s Trust and the Refugee Council 2006

| ማድረግ ያለብዎት ነገር | ማድረግ የሌለቦት ነገር |
| --- | --- |
| ከመጀመርዎ በፊት ቢያንስ ለ 3 አመት ያህል የመኖርያ ፈቃድ እንዳልዎት ለመረጋገጥ መጣር አለብዎት። ይህም ብድር ለማግኘትና እንዲሁም የሚቀጥለው የኢሚግሬሽን ጉዳይ ከመድረሱ በፊት ስራዎን እንዲጀምሩ ይረዳዎታል። | የመኖርያ ፈቃድዎ ጊዜ ወደማለቁ የንግድ ስራዎን ለመጀመር አያስቡ። ምክንያቱም ስራዎን ለመጀመር የሚጠይቁቸውን እርዳታዎችና ብድርም ጭምር ለማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆን። |

**ተጨማሪ መረጃ የት ለማግኘት ይችላሉ፤**

ስለ የኢምግሬሽን ሁኔታ በተመለከተ የሆነ ዓይነት ጥያቄ ካልዎት፡ ቀጥሎ ያሉትን ዌፕሳይቶች ይመልከቱ፡

→ ረፍዩጂ ካውንስል (Refugee Council)
  www.refugeecouncil.org.uk
→ የኢሚግሬሽን የምክር አገልግሎት (Immigration Advisory Service)
  www.iasuk.org.uk
→ የስደተኞች የህግ ማእከል (Refugee Legal Centre)
  www.refugee-legal-centre.org.uk
→ የኢሚግሬሽን የዜግነት ክፍል
  (Immigration Nationality Department)
  www.ind.homeoffice.gov.uk
→ የዜጎች የምክር ጽሕፈት ቤት (Citizens Advice Bureau)
  www.adviceguide.org.uk/index/your_rights/immigration
→ ለስራ ማብቂያ መድረክ (Employability Forum)
  www.employabilityforum.co.uk

# ደረጃ 3: የራስዎን CV (የትምህርትና የስራ ልምድ መረጃ ታሪክ) ማዘጋጀት

ሲቪ (CV) ስላልዎት የስራ ልምድና የትምህርት ደረጃ በዝርዝር መረጃ የሚያቀርብ ጽሁፍ ነው። እንግሊዝ አገር ውስጥ ማንኛውም ስራ ፈላጊም ይሁን ንግድ ለመጀመር እርዳታ የሚፈልግ ሰው በቅድሚያ ይህንን ሲቪ ማዘጋጀት አለበት። ከዚህ ቀጥለው አንዳንድ ሲቪዎች ለማዘጋጀት የሚያግዝዎት ነጥቦች ተዘርዝረዋል።

| |
|---|
| ተማሪ ባሉበት ወይም ስራ በሚሰሩበት ጊዜ፣ የሆነ ያልተጠቀሙበት ግዜ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን በሲቪዎ የንግድ ስራውን ለመጀመር እንደሚችሉ ካሳዩ ለምሳሌ፣ እንደ የባጀቲንግ፣ ማርኬቲንግና ሰዎችን የማስተዳደር ችሎታ እና ጥሩ መሪነት እንዳልዎት ወዘተ ካሳዩ ምንም ችግር አይኖረውም። |

ቀጥሎ ካሉት ደግሞ እርዳታ ለማግኘት ይችላሉ፣

→ የራሳቸውን ሲቪ የጻፉ ጓደኞች ወይም ቤተሰቦች
→ የስራ ምክር የሚሰጡ ማህበሮች፣ ነገር ግን ለዚህ አገልግሎት ይከፍላሉ፣
→ የአከባቢው የበጎ አድጊ ወይም የስደተኛ ማህበሮች ነጻ ምክር ሊሰጥዎት ይችላሉ፣

**ያለፉት የትምህርት ደረጃ**
ስለተማሩት ትምህርት (ትምህርት ቤት፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ) እንዲሁም ስለወሰዱት ስልጠና በቅደም ተከተል (የጊዜ) ያጠናቀቁትን የትምህርት ደረጃ ይጻፉ።

አንዳንድ ጊዜ ብቃትዎን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ፥

→ **ሰርቲፊኬትዎ ከርስዎ ጋር ካለና** ከአገርዎ ሲመጡ ይዘዉት የገቡትን የምህርት ደረጃ እንግሊዝ አገር ውስጥ ተቀባይ እንዲያገኝ ከፈለጉ የእንግሊዝ ብሔራዊ የመረጃ ማጽደቅያ ማእከል (National Recognition Information Centre for the United Kingdom (UK NARIC)) ድረስ በመሄድ ይህን አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። ይህም እንዲሰራልዎት የምስክር ወረቀቶችዎን ማቅረብና ለአገልግሎቱም መክፈል ያስፈልግዎታል።
→ **በምስክር ወረቀት የተረጋገጠ የብቃት ሰርቲፊኬትዎ ከእርስዎ ጋር ከሌለ ደግሞ** ያለፉትን የትምህርት ታሪክዎ ዘርዝረው ይጻፉ። ስራ ለመጀመር እርዳታ የሚሰጥዎትን ድርጅት (ደረጃ 9) ስለዚህ ጉዳይ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ይጠይቁ።

 © The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

| |
|---|
| ማስታወሻ፤ ምንም እንኳን ጥሩ የትምህርት ደረጃ አስፈላጊ ቢሆንም፡ ደረጃዎ ዝቅተኛ ከሆነ መጨነቅ አይገባም፡ ምክንያቱም ንግድ ለመጀመር የሚተባበሩ ድርጅቶች የሚያዩት ንግድን ለመጀመር ጥሩ ችሎታ ካልዎት ነው። |

**የስራ ልምድዎ የሚገልጽ ዝርዝር**

ከዚህ በፊት የሰሯቸውን ስራዎች በየጊዚያቸው ቅደም ተከተልና ከነ መግለጫቸው ዘርዝረው ያስቀምጡ። ይህ የሰሩት ስራ ዝርዝር ታሪክ ይባላል። በዚህም መሰረት የንግድ ስራ ለመጀመር ልምድ ካልዎት ማየት ይቻላል። ከዚህ በፊት የንግድ ስራ የማቋቋም ልምድ ከነበርዎት በዚህ ነጥብ ላይ አተኩረው መጻፍ እንዳለብዎት አይርሱ።

→ እንግሊዝ አገር ውስጥ አብዛኛው ጊዜ ሁለት የአሰሪ ምስክርነቶች እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ምስክርነቱ ባለፉት አሰሪዎችዎ የሚጻፍ አጠር ያለ ደብዳቤ ሆኖ ስለሰሩዎቸው ስራዎችና ምን ያህል ውጤታማ እንደነበሩ የሚገጽ ነው።

→ ያለፉት አሰሪዎችዎ ከእንግሊዝ አገር ውጭ የሚኖሩ ከሆነ ወይንም ማግኘታቸው ከባድ ከሆነ ይህንኑ ዓይነት ደብዳቤ ለማስጻፍ አስቸጋሪ ይሆናል። ሌላ የሚያስፈልግዎትን ልምድ ለማግኘት የሚችሉበት መንገድ ባሉበት አከባቢ ያሉት የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ያለክፍያ በፍቃድዎ መስራት ነው። (ከታች ያለው እና ደረጃ 6 ይመልከቱ)

→ በሰሩት ስራ መሃል ስራ ያቆሙበት ጊዜ ካለ ስራ ለመጀመር እርዳታ ከሚሰጥዎትን ድርጅት (ደረጃ 9) ስለዚህ ጉዳይ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ምክር ይጠይቁ።

**የበጎ ፍቃድ ስራ**

ከዚህ በፊት ያለ ክፍያ በፍቃደኝነት የሰሯቸውን ስራዎች ደግሞ አስፈላጊ ናቸው። ለምሳሌ፡ በአከባቢዎ ያለው የህብረተሰብ ፕሮጀክቶች ውስጥ ወይንም ከማንኛውም የንግድ ድርጅት ጋር የሰሩት ስራ ምን ያህል የስራ ልምድ እንዳልዎት ሊያሳይ ይችላል።

| ማድረግ ያለብዎት ነገር | ማድረግ የሌለቦት ነገር |
|---|---|
| በስራ ልምድ መልክ ያገኙትን እየንዳንዱ ነገር ለመጻፍ ይሞክሩ። በተጨማሪም በትውውቅ ያለ ክፍያ የሰሩላቸውን ሰዎች ለማስታወስ ይሞክሩ። ከነዚህም ሰዎች የስራ ምስክርነት ደብዳቤ ማስጻፍ ይችላሉ። | የሚፈለገው የስራ ልምድ ወይንም ትምህርት ማረጋገጫ የለኝም ብለው መጨነቅ የለብዎትም። ይህ ለብዙ ስደተኞች የሚያጋጥም ችግር ነው።. |

## ተጨማሪ መረጃ የት ለማግኘት ይችላሉ፤

→ የአከባቢው የስራ ፍለጋ ማእከል (Jobcentre Plus)፡ የራስን ንግድ ለመጀመር የሚረዳ ምክር ያቀርባል፡ በተጨማሪም ሲቪን በደንብ እንዲጽፉት ሊተባበርዎት ይችላል፡ www.jobcentreplus.gov.uk

→ በሌላ መንገድ ደግሞ፡ ኢንተርነት ላይ ስለ ሲቪ አጻጻፍ የሚገልጹ ብዙ ዌብሳይቶች ሊያገኙ ይችላሉ፡ለምሳሌ www.bbc.co.uk/radio1/onelife/work/index.shtml?cvs/ ወይም www.workthing.com ወይም http://jobsadvice.guardian.co.uk/

→ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ብዌፕሳይታቸው ስለ ሲቪ አጻጻፍ ምክር ያቀርባሉ፡


© The Prince’s Trust and the Refugee Council 2006

## ደረጃ 4: በእንግሊዘኛ ቋንቋ በደምብ ለመግባባት እንዲችሉ እርዳታ ማግኘት

በየእለቱ ኑሮና እንዲሁም በንግድ ስራ ላይ በደምብ የመግባባት ችሎታ እንዲኖርዎት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፡ ይህ ቀጥሎ ያሉትን ለማድረግ ይጠቅማል፡

- → የንግድ ስራ እቅድ ለመጻፍ
- → ብድር ከሚሰጥዎት ድርጅት ጋር ለመደራደር ወይም ለሽያጭ እቃዎች ለሚከፈለው ግብር (Value Added Tax - VAT) ለመመዝገብ

በእያንዳንዱ የንግድዎ ክፍል ላይ ይሚካሄዱትን ሁኔታዎች በደንብ ማወቅ መቻልዎ በጣም አስፈላጊ ነው።

**እርዳታ የት ማግኘት እንደሚችሉ**

የእንግሊዘኛ ትምህርቱ እንግሊዘኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች (English for Speakers of Other Languages (ESOL)) ተብሎ ይጠራል። ይህ ትምህርት ደግሞ ለጥገኝነት ጠያቂዎችና ስደተኞች እስከ ነሐሰ 2007 በነጻ ይሰጣል።

- → **ላልተወሰ ጊዜ እንዲቆይ ፍቃድ (leave to remain)** (ይህ ማለትም፡ የስደተኛ ተቀባይነት፡ የበጎ አድራጎት ከለላ ወይም ጊዝያዊ የመኖርያ ፍቃድ) ካልዎት ነጻ የESOL ትምህርት የማግኘት መብት አልዎት።
- → ነገር ግን **ከ19 ዓመት በላይ የሆኑት ጥገኝነት ፈላጊዎች በሙሉ** ለዚህ ትምህርት ሊከፍሉ ይገደዳሉ። አንዳንድ ማህበሮች በነጻ ወይም በቅናሽ ዋጋ ትምህርቱን ሊሰጡ ይችላሉ።

በአከባቢዎ ከሚገኙት ቤተ መጻሕፍት፡ የስደተኛ ማህበሮችና የስራ ፈላጊ ማእከል (Job Centre) ወይንም Learndirect ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚሰጠው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ESOL ስለሚያስተምሩ ድርጅቶችን አስፈላጊ መረጃ ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም ይህን መረጃ ቀጥለው በተዘረዘሩት ይገኛሉ፡

- → ከሁለተኛ ደረጃ ተጨማሪ ትምህርት የሚሰጡ ኮሌጆች
- → ለጎልማሶች ትምህርት የሚሰጡ ኮሌጆች
- → ዩኒቨርስቲዎች
- → በፍቃድ የሚሰሩና ለህብረተሰብ ድጋፍ የሚቋቋሙ ድርጅቶች
- → የLearndirect በኢንተርኔት የሚገኙ ማእከሎች
- → በግል ትምህርት ቤቶች

## ለንግድ ስራ የሚያስፈልግ እንግሊዘኛ

ብዙ ተጨማሪ ትምህርት የሚሰጡ ኮሌጆች ለንግድ ስራ የሚያስፈልግ እንግሊዘኛ ያስተምራሉ፤ ለዚህ ግን ሊያከፍልዎት ይችላሉ። በአከባቢዎ የሚገኙት የአከባቢው የድርጅት ወኪል፡ የአከባቢው ምክርቤት ወይንም ባለስልጣን ትምህርቱ የት እንደሚሰጥ ሊያስረድዎት ይችላሉ።

(ሌሎች የአከባቢ ማህበሮችም ሊኖሩ ይችላሉ፡ ለምሳሌ የስደተኛ የትምህርትና የስልጠናና የምክር አገልግሎት (Refugee Education and Training Advisory Service - RETAS) እና የረፍዩጂ ካውስል (Refugee Council) ለንግድ ስራ የሚያስፈልግ እንግሊዘኛ ስለሚያስተምሩ በአካባቢዎ ቅርንጫፍ ካላቸው ይጠይቁ።)

→ የሚኖሩበት ሕብረተሰብ ውስጥ ከእርስዎ የተሻለ ለንግድ ስራ የሚያስፈልግ እንግሊዘኛ የሚያውቅ ሰው ካለ እርዳታ ይጠይቁ
→ የጽሑፍና የቃል ትርጉም አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች (የአከባቢው ምክርቤት ወይንም ሕብረተሰቡን ለመርዳት የሚቋቋሙ ድርጅቶች ይጠይቁ) ህጋዊ የሆኑ ጽሑፎችን ለመተርጎም ይረድዎታል። ይህን አገልግሎት ለማግኘት የሚችሉት ከፍለው ሊሆን ይችላል።

 © The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

| ማድረግ ያለብዎት ነገር | ማድረግ የሌለቦት ነገር |
| --- | --- |
| ከተቻለ ለቋንቋ ትምህርት ይመዝገቡ። ይህን ለማደረግ ካልቻሉ ደግሞ፡ በተቻለ መጠን መደበኛ የሆነ እንግሊዘኛ መጠቀም ይገባል። እንግሊዘኛ ቋንቋ በደምብ ከቻሉ ከሌላ ሰው ጥገኝነት ተላቀው የንግድ ስራዎን ይበልጥ ለማሳካት ያስችልዎታል።ከተቻለ ለቋንቋ ትምህርት ይመዝገቡ። ይህን ለማደረግ ካልቻሉ ደግሞ፡ በተቻለ መጠን መደበኛ የሆነ እንግሊዘኛ መጠቀም ይገባል። | ምንም እንኳን ከሌሎች ሰዎች ጠቃሚ ምክር ሊያገኙ የሚችሉ ቢሆኑም፡ ብዙ እርዳታ አይጠብቁ። ሁሉም የግድዎ ክፍል እንዴት እንደሚንቀሳቀስ ራስዎ መገምገም መቻል አለብዎት። |

**ተጨማሪ መረጃ የት ለማግኘት ይችላሉ፤**

→ Learndirect www.learndirect.co.uk
→ በአካባቢዎ ያሉት ከሁለተኛ ደረጃ ተጨማሪ ትምህርት የሚሰጡ ኮሌጆች
→ የአካባቢዎ የስራ ፍለጋ ማእከል (Jobcentre Plus) የ ESOL ድጋፍ የት ለማግኘት እንደሚችሉ ይነግርዎታል። www.jobcentreplus.gov.uk
→ የስደተኞች የምክርና መመርያ ክፍል (Refugee Advice and Guidance Unit) ለስደተኞች የሚሆን ስልጠና በተመለከተ ምክር ያቀርባል፡ www.londonmet.ac.uk/ragu/home.cfm
→ RETAS ድርጅት ለማቋቋም ትምህርት ይሰጣል፡ www.education-action.org
→ ረፉዩጂ ካውንስል (Refugee Council) ለንግድ የሚሆን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ያቀርባል፡ www.refugee-council.org.uk
→ የአከባቢው ቤተ መፃህፍት
→ የዜጎች የምክር ጽሕፈት ቤት (Citizens Advice Bureau) www.citizensadvice.org.uk
→ በአከባቢዎ የሚገኝ ባለስልጣን/ምክር ቤት (ትምህርት ክፍል/ሚኒስቴር)

# ደረጃ 5: መደበኛ የሆነ የንግድ ስራ ስልጠና ማግኘት

እንግሊዝ አገር ውስጥ ለንግድ ስራ ጀማሪዎችን ተብለው የተዘጋጁ የተለያዩ ስልጠናዎች አሉ። እነዚህ ስልጠናዎች፡

→ እንግሊዝ አገር ውስጥ ለራስዎ የስራ እድል መፍጠርን ያስተምራሉ
→ ችሎታዎን ለይቶ ለማወቅ ይረድዎታል
→ የመጀመሩ ሂደት ምን እንደሆነ የበለጠ ማብራርያ ይሰጥዎታል
→ ለመጀመር የሚያስፈልጉት ዝግጅቶችን አስመልክቶ ገለጻ ይሰጥዎታል
→ የንግድ ስራ እቅድዎን ለመጻፍ ይረድዎታል
→ የሚጠበቅብዎትን የግብር፡ VAT፡ እንዲሁም የብሄራዊ ዋስትና (National Insurance) ቁጥሮችን አስመልክቶ ገለጻ ይሰጥዎታል፡
→ ከሌሎች እንደ እርስዎ ተመሳሳይ የንግድ ስራ የመክፈት ፍላጎት ካላቸው ሰዎች ጋር ለመገናኘትና ለመተጋገዝ ያስችልዎታል።

ክፍያ እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ ነገር ግን፡ ሊማሩት የሚገባዎት ስልጠናዎች ከሆኑ ክፍያውን ከፍሎ መማር ለመጪው ከፍተኛ ጥቅም ኣለው። የተለያዩ ድርጅቶች ለስደተኞች የንግድ ስራ ስልጠና ይሰጣሉ። የአካባቢዎ የስደተኞች ወኪሎች ወይም ድርጅቶች በሚኖሩበት አከባቢ የሚገኙ ስልጠናውን ስለሚሰጡት ድርጅቶች ሊያውቁ ይችላሉ።

 © The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

**ተጨማሪ መረጃ የት ለማግኘት ይችላሉ፤**

→ የንግድ ስራ ስልጠና የሚሰጡ ስራ አስጀማሪ ወኪሎች ዝርዝር The Prince's Trust <ለጀማሪዎች መምሪያ ቁጥር 12 - የእርዳታ ምንጮች> የሚለውን ጽሁፍ ይመልከቱ

→ RETAS ስራ ላላገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች የንግድ ስራ ጀማሪዎችን የሚረዱ ትምህርቶች ይሰጣሉ። ድርጅቱ የሚረዳቸው ሰዎች (ሀ)የራሳቸው ስራ መክፈት ለሚፈልጉት ወይም (ለ)ከሌሎች በማህበር ከተቋቋሙ ሰዎች ጋር በመተባበር (አብዛኛው ጊዜ ለንደን ውስጥ)ለመስራት ሃሳብ ላላቸው ነው። www.education-action.org

→ ረፉዩጂ ካውንስል (Refugee Council) እንግሊዝ አገር ውስጥ ስደተኞች የስራ ገበያ ውስጥ እንዲገቡ የሚያበረታታ ድርጅት ነው፡ www.refugeecouncil.org.uk

→ የማህበረሰብ የእንቅስቃሴ ማህበር ሀ ለንደን ውስጥ ላሉ ስደተኞች የንግድ ስራ ትምህርት ይሰጣል፡ www.can-online.org

→ የንግድ መገናኛ (Business Link) የተባለ የህዝብ ድርጅት ለመለስተኛና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች የስራ ምክር ይሰጣል። የዚህ ድርጅት አሰራር በየቦታው ባሉት የመገናኛ መስመር ተቋሞች በኩል ነው። በአካባቢዎ ላይ ካሉ ይፈልጓቸው። www.businesslink.gov.uk

→ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ወኪል (United Nations Refugee Agency (UNHCR)) ስደተኞች በኢንተርኔት 'Refugees Online' በሚባለው ፕሮጀክቱ መንገድ ስደተኞችን ሊረዱ የሚችሉ የድርጅቶችን ስም ዝርዝር አዘጋጅቷል፡ www.refugeesonline.org.uk

# ደረጃ 6: ባሉበት አከባቢ ወይም በማህበረሰቡ ያሉት የንግድ ድርጅቶች ውስጥ የበጎ ፍቃድ ስራ መስራት

የበጎ ፍቃድ ስራ የሚባለው በነጻ ያለክፍያ መስራት ማለት ነው። አከባቢዎ ከሚገኙት ድርጅቶች ወይም ኮሚኒቲ የበጎ ፍቃድ ስራ ለመስራት ማሰብ አለብዎት። ይህ ስራ ደግሞ ቀጥሎ ላሉት ነገሮች እንዲያገኙ ይጠቅሞታል፤

→ ሊጀምርዎት የሚፈልጉት ስራ ላይ ተጨማሪ የስራ ልምድ ሊያገኙ ይችላሉ፣
→ ልዩ የሆነ ችሎታ እንዲያዳብሩ ይረዳል
→ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታዎ ሊያዳብሩ ይችላሉ፣
→ በየስራ ልምድዎ ጽሑፍ (CV) ላይ እንግሊዝ አገር ውስጥ የስራ ልምድ እንዳልዎት ለመገልጽ ይችላሉ፣
→ ስለስራው ምስክር /ሪፈረንስ/ ሊያገኙ ይችላሉ። የስራ ባልደረባዎ ይህን የምስክር ደብዳቤ ደስ እያላቸው ሊጽፍሎት ይችላሉ።

**የጥገኝነት ጠያቂ (asylum seeker) ቢሆኑም ወይም እንዲቆዩ ፍቃድ (Leave to Remain) ለማግኘት የሚጠብቁ ቢሆኑም የበጎ ፍቃድ ስራ ለመስራት ይችላሉ።**

የበጎ አድራጎት ስራ ለመስራት ዕድል ማግኘት፣

→ ማንኛውም ድርጅት ያለው የሚያውቁት ሰው ከለ፣ የበጎ ፍቃድ ስራ እንዲሰሩ በመጠየቅ፣
→ ሊጀምሩት የሚፈልጉትን የንግድ ዓይነት ስራ ያላቸው ድርጅቶችን ማነጋገር፣
→ ሊሰሩበት የሚችሉ ማንኛውም ዓይነት የኮሚኒትዩ ፕሮጀክት ካለ መጠየቅ፣

 © The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

**ቀጥሎ የተዘረዘሩት ድረገጾች ላይ ተጨማሪ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ፤**

- ብሔራዊ የበጎ ስራ ማእከል (National Centre for Volunteering) www.volunteering.org.uk
- Reach www.volwork.org.uk
- ረፍዩጂ ካውንስል (Refugee Council) www.refugee-action.org.uk
- Refugee Council www.refugeecouncil.org.uk
- RETAS www.education-action.org
- Timebank www.timebank.org
- የእንግሊዝ አገር የበጎ አድራጎት ስራ እድገት (Volunteer Development England) www.vde.org.uk
- The Prince's Trust www.princestrust.org.uk

# ደረጃ 7: ልጅችዎ የሚቆዩበት ቦታ ማዘጋጀት

ልጆችዎን ራስዎ የሚንከባከቡ ከሆኑ እና የራስዎ ንግድ ለመጀመር እያቀዱ ከሆነ ልጆችዎን ትተው የሚሄዱበት ቦታ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ትተው ለመሄድ ይፈልጋሉ።

ስለዚህ ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች ለማድረግ ይችላሉ፡
→ ጓደኛዎ ወይም ቤተሰብችዎ እንዲጠብቁሎት ለመጠየቅ ይችላሉ፡
→ የአከባቢው መዋእለ ህፃናት ማህብሮችን፥ ልጆችዎን ከማያውቁት ሰው ጋር ትተው ለመሄድ ደስ የማይሎት ከሆነ፡ የህፃናቶች እንክብካቤ ባለሙያ (registered childminder) የሆነ ሰው መፈለግ ይገባል። እነዚህ የህፃናቶች እንክብካቤ ባለሙያ የሚባሉት፤
  - ብቃት/ትምህርት አላቸው
  - ከነሱ ጋር ጊዜ እንዲያሳልፉና ልጆችዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ ራስዎ ለማየት ይፈልጋሉ።
  - ከነሱ ጋር ጊዜ እንዲያሳልፉና ልጆችዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ ራስዎን ለማየት ይፈልጋሉ።
→ በ የስራ ቀረጥ እርዳታ (Working Tax Credit) የሚባለው የመንግስት ፕሮጀክት አማካኝነት ለመዋእለ ህፃናት የሚሆን እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ። (ለዝርዝር መረጃ እታች ይመልከቱ)
→ ባለሙያዎች ከሆኑት ለቤተሰብ ብድር የሚሰጥ መስመር (Lone Parent Helpline) የሚመሩት እንደ ብቸኛ ወላጆች ቤተሰቦች (One Parent Families) ድርጅቶችን ለመጠየቅ ይችላሉ። ቴሌፎን - 0800 0185 026
→ የመጀመር ድጋፍ (ደረጃ 9) የሚፈልጉ ከሆነ ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ ይገባል።

 © The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

## ተጨማሪ መረጃ የት ለማግኘት ይችላሉ፤

- የሰራተኛ የቀረጥ እርዳታ መስመር (Working Tax Credit Helpline) (እንግሊዝ አገር፡ ዌልስ፡ ስኮትላንድ) 0845 300 3900/ (ሰሜናዊ አየርላንድ) 0845 603 2000
- Sure Start የሚባለው የመንግስት ፕሮግራም ዓላማ፡ ማንኛናውም ህፃን ጥሩ እድል እንዲያገኝ ነው። ስለሆነ እንግሊዝ አገር ውስጥ ስለሚገኙት መዋእለ ህፃናቶችና ወጪዎችን በተመለከተ እርዳታ እንዴት ለማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ያቀርባል። www.surestart.gov.uk ወይም www.childcarelink.gov.uk
- ብቸኛ ወላጆች ቤተሰቦች (One Parent Families) ፡ይህ ብቸኛ የሆኑ ወላጆችን ይተባበራል፡ www.helpdesk.oneparentfamilies.org.uk (እንግሊዝ አገር፡ ዌልስ) www.opfs.org.uk (ስኮትላንድ)
- Gingerbread ብቸኛ ወላጆች ቤተሰቦች የሚሆን ኔትዎርክ አለው፥ www.gingerbread.org.uk
- የመዋእለ ህፃናት የገንዘብ እርዳታ (Daycare Trust) የሚባለው ብሔራዊ የመዋእለ ህፃናት የበጎ አድራጎት እርዳታ ነው። ዌፕሳይታቸው ደግሞ ተጨማሪ ስለ መዋእለ ህፃናት መረጃ ያቀርባል፤ www.daycaretrust.org.uk
- ብሔራዊ የመዋእለ ህፃናት ማህበር (National Day Nurseries Association) (NDNA) የሚባለው ፕሮግራም ዓላማው ለትናንሽ ህፃናቶች ብልጽግናና ትምህርት ለማዳበር የሆነ ብሔራዊ የበጎ አድራጎት ማህበር ነው፡ www.ndna.org.uk
- ብሔራዊ የህፃናት አስተዳደግ ማሕበር (The National Childminding Association) (NCMA) የሚባለው ደግሞ በእንግሊዝ አገርና በዌልስ የሚገኝ ብሔራዊ የበጎ አድራጎትና ለአባልነት ፍቃድ ያላቸው የህፃናቶች እንክብካቤ ባለሙያ ማህበር ነው። www.ncma.org.uk
- የቅድመ ትምህርት ቤት ትምህርት ማህበር (The Pre-school Learning Alliance) የትናንሽ ህፃናቶች ትምህርታዊ የበጎ አድራጎት ማህበር ነው፡ www.pre-school.org.uk

# ደረጃ 8: የሚያስፈልግዎትን ገንዘብ ማደራጀት

**የባንክ ሂሳቦች**
የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ከፈለጉ፡ የመታወቂያ ወረቀት ያስፈልጎታል። ባንኮች ፓስፖርትዎ (passport)፡ የመንጃ ፍቃድዎ ወይም ሂሳብ የሚከፍሉበት ደረሰኝ (ለምሳሌ፡ የመብራት ወይም ውሃ) ለማየት ይፈልጋሉ።

እነዚህ ዓይነት ወረቀቶች ከሌልዎት፡ ባንኩን ሌላ የመታወቂያ ወረቀትን ለምሳሌ ህጋዊ የሆነ የመኖርያ ፍቃድ (Leave to Remain) ወይም ሌላ የሆም ኦፊስ (Home Office) ወረቀት የሚቀበል መሆኑን ሊጠይቁት ይገባል።

በሌላ በኩል ደግሞ **ካረንት** (current) ከሚባለው ይልቅ **በይዚክ** (basic) የሚባለውን የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ሊቀልዎት ይችላል። በሁለቱም ዓይነት ሂሳቦት፡ **በካረንት** (current) እና **በበይዚክ** (basic) ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች ለማድረግ ይችላሉ፤

→ በካሽ ማሽን ሊጠቀሙበት የሚችሉ የካሽ ካርድ ማግኘት
→ ገንዘብንና ሂሳቦችን ለመክፈል
→ ነገር ግን፡ በካረንት (current) የሚባለው የባንክ ሂሳብ ላይ አስቀድመው የተስማሙበትን (<የባንክ እላፊ እዳ>) (‘overdraft’) ብቻ ይፈቀድሎታል፡

*ይህ የባንክ እላፊ ዕዳ የሚባለው (overdraft)፡ ባንክ ውስጥ ካልዎት ገንዘብ በላይ ተጨማሪ ገንዘብ መጠቀም ማለት ነው።(ባንኩ ያበድርዎታል) ባንኩ ለዚህ አገልግሎት ወለድና ሌሎት ክፍያዎችን ያስከፍላል፡ (የገንዘብ አገልግሎት ባለስልጣን (Financial Services Authority (FSA), 2006).*

ነገር ግን **በይዚክ** (basic) የሚባለው ሂሳብ፡ ባንኩ ከ £10 ገንዘብ በላይ እንዲያወጡ አይፈቅድሎትም። በተጨማሪም ባንኩ ታማኝነትዎን በተለይም የባንክ ቸኮችን በተመከተ ያልዎትን ታሪክ በማየት፡ የ **ካረንት** (current) ባንክ ሂሳብ ሊከፍትሎት ወይም ሊያበድርዎት ይችላል። ማለትም፡

→ የነበርዎትን የተለያዩ የባንክ ሂሳቦችን በመመልከት እና
→ የሆነ ያልተከፈለ ዕዳ ካልዎት በማጣራት

 © The Prince’s Trust and the Refugee Council 2006

ሆኖም ግን ባንኮቹ፡ እርስዎ ከሌላ አገር ስለመጡ ታማኝነትዎን ለማረጋገጥ ስለማይችሉ፡ አዲስ **የካረንት** (current) የባንክ ሂሳብ ሊሰጥዎት ከባድ ሊሆን ይችላል። ስለሆነ ባንኩ የባንክ ሂሳብ ለመክፈት እምቢ ካልዎት ደግሞ ሌላ **በይዚክ** (basic) የባንክ ሂሳብ እንዲከፍትሎት ይጠይቁ።

ማንኛውም ዓይነት የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ካስቸገርዎት፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ የተባበሩት በኣከባቢዎ ለሚገኙ ለረፍዩጂ ማህበሮች ወይም የዜጎች የምክር ቤቶች ቢሮ (Citizens Advice Bureau) ሄደው ለማነጋገር ይችላሉ። ሌሎት ሊረዳዎት የሚችሉ ማህበሮች ቀጥሎ ባለው ገጽ ሊያገኙ ይችላሉ።

**እስላማዊ እምነትና ገንዘብ**

የእስልምና እምነት ተከተይ ከሆኑ፡ ንግድዎን ከመጀመርዎ በፊት <ሪባ> 'riba' የሚባለውን ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል። ይህ <ሪባ> 'riba' የሚባለው ወለድ መስጠት ወይም መቀበል ማለት ነው። ምክንያቱም ይህ ሪባ እንደ ሓራም (gharar) ስለሚቆጠር በሸሪዓ ሕግ አይፈቀድም።

ይህን ችግር እንዴት ሊፈቱት ይችላሉ?

→ የራሳቸውን ንግድ የጀመሩት ጓደኞችዎን፡ ቤተሰብዎን ወይም የኮሚኒቲይ አባሎችን መጠየቅ ይችላሉ፡
→ የሸሪዓ ሕግ የሚያከብሩ አንዳንድ ባንኮች ወይም ማህበሮች ስለሚገኙ ሊተባበርዎት ይችላሉ።

**የሸሪዓ ህግ ከሚያከብሩ ማህበሮች/ባንኮች ጥቂቶቹ፡**

የእንግሊዝ አገር የእስልምና ባንክ (Islamic Bank of Britain) የሸሪዓ ህግ የሚከተል ባንክ ነው።

የHSBC የሚባለው ማህበር በ አማናህ ክፍል (Amanah division) በ2003 የተከፈተ ሆኖ፡ ለሁሉም እስላሞች የቤት ለመግዛትና የገንዘብ እርዳታና ግላዊ የባንክ ሂሳቦች አገልግሎት የሚያቀርብ ነው። ስለሆነ በአሁኑ ግዜ ንግድ ለመጀመር የሚፈልጉ ሰዎች እንዴት ለመረዳት እንደሚችል እየሰራ ይገኛል።

The Prince's Trust ይህ ማህበር ወጣት እስላሞች ቀስ ብለው የሚከፍሉት የገንዘብ ብድር ለመስጠት ዋና ከሆኑት የሸሪዓ ምሁራንን ምክር ጠይቀዋል። ውጤቱ ደግሞ የሚከፍሉት ገንዘብ ወለድ ጨምሮ ሳይሆን ለመደበኛው የጽሕፈት ቤት ክፍያ ብቻ እንደሚሆን ተወስነዋል።

**ተጨማሪ መረጃ የት ለማግኘት ይችላሉ፡**

- → FSA (Financial Services Authority) (የገንዘብ አገልግሎት ባለስልጣን) ፡ ዌፕሳይቱ ስለ ተራ የባንክ ሂሳብ መረጃ ያቀርባል፡ www.fsa.gov.uk
- → የዜጎች የምክር ቢሮ (Citizens Advice Bureau) www.citizensadvice.org.uk
- → Islamic Bank of Britain www.islamic-bank.com
- → ስለ HSBC Amanah ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፡ www.hsbcamanah.com ላይ ያንብቡ
- → ንግድ መጀመር መመርያ 2 — ንግድን መጀመር - ይህ መመርያ የመጀመርያ ብድር እንዴትና የት ለማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ያቀርባል። www.refugeesintobusiness.org.uk/guide
- → ንግድ መጀመር መመርያ 12 — የእርዳታ ምንጭ - የገንዘብ እርዳታ የት እንደሚያገኙ ይዘረዝራል፡ ቀጥሎ ያለውን ዌፕሳይት ይመልከቱ www.refugeesintobusiness.org.uk/guide

 © The Prince’s Trust and the Refugee Council 2006

# ድረጃ 9: ከንግድ ስራ ባለሞያ ንግድ የመጀመር ድጋፍ ማግኘት፣

እንግሊዝ አገር ውስጥ ይህ የስራ መጀመር የድጋፍ ምክር የሚያቀርቡ ብዙ ማህበሮች ይገኛሉ፣ እነዚህም አብዛኛው ጊዜ ምክር በመስጠትና በቀጥታ ስልጠና በመስጠት ይሰራሉ። ሊጀምሩት ያቀዱትን ስራ ለእርስዎ ይሆናል ወይም አይሆንም ለሚለው ጥያቄና እንዴት ስራው ሊያከናውኑት እንደሚችሉ ለመወሰን ይረዳዎታል። ይህ ፕሮፌሽናል ለስራ ጀማሪዎች የማያዳላ ምክርና እርዳታ የሚያቀርብ ምንጭ ነው።

**የስራ መጀመር ድጋፍ የሚያቀርቡ ማህበሮች፣**
ቀጥሎ የተዘረዘሩት አገልግሎቶች የሚያቀርቡ እና ስራ ለመጀመር እርዳታ የሚሰጡ የተለያዩ የመንግስት፣ የግልና የበጎ አድራጎት ማህበሮች ይገኛሉ።

→ የራስን ንግድ እንዴት ለመጀመር እንደሚቻል የሚገልጹ ምክሮችንና መመርያዎችን ማቅረብ
→ የስራ ስልጠና ትምህርቶች መስጠት
→ የስራ እቅድ ለማውጣት እርዳታ ማቅረብ
→ ስለ ኔትወርኪንግ ሂደቶች መረጃ ማቅረብ

ከተጠቀሱት አንዳንድ አገልግለቶች በነጻ ይሰጣሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ስለሚያስከፍሉ፣ ከአገልግሎታቸው ከመጠቀምዎ በፊት ማረጋገጥ ይገባል።

**የንግድ አማካሪ**
ይህ የንግድ አማካሪ የሚባለው ምክር የሚሰጥ ነው፣ ለምሳሌ፣ የስራ እቅድ በመጻፍ ላይ፣ ህጋዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይና ያልዎትን ካፒታል ማስተዳደር የመሳሰሉ ምክር ያቀርባል። አብዛኛቹ የንግድ አማካሪዎች ሞያዊ የሆነ ስልጠና የወሰዱና ብዙ የስራ ልምድ ያላቸው ናቸው። የተወሰኑ ችግሮችን ለመፍታት ይረድዎታል እንዲሁም በተወሳሰበ ሁኔታ ላይ እርዳታ ሊያቀርብሎት ይችላሉ። የነዚህ አማካሪዎች ደግሞ ለአጭርጊዜ እንዲሁም ረዘም ላለ ጊዜ እርዳታ ይሰጣሉ። እነዚህ አገልግሎቶች ለማግኘት እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ። ቢዝነዝ ሊንክ (Business Link) በሚለው ዌብሳይት ላይ ‘Choose and manage a business adviser’ (የንግድ አማካሪ መምረጥና መፈለግ) በሚል አርእስት አስመልክቶው የተጻፋት የመመርያ ጽሁፎች ሊያገኙ ይችላሉ (እታች ይመልከቱ)።

**በንግድ አማካሪና የንግድ አርአያ ያለው ልዩነት ምንድን ነው**
የንግድ አማካሪ ባለሞያ ሲሆን የባለሙያ ምክር ያቀርባል። የንግድ አርአያ የሚባለው ግን፣ አብዛኛው ጊዜ በበጎ ፍቃድ በነጻ የሚሰራ ሆኖ፣ ጠቅላላ የሆነ የንግድ ፕላንና ሃሳቦችንና ችግሮችን በተመለከተ ምክር ያሰጣል።

## የንግድ አርአያ የሚሆን ሰው

ይህ የንግድ አርአያ የሚባለው፣ ገና አዲስ ንግድ በመጀመር ላይ ለሚገኙት ሰዎች መደበኛ የንግድና ግላዊ መመርያዎች ያቀርባል። የዚህ የንግድ አርአያ ሰው ዓላማ፣ ለእርስዎ ቀጣይነት ያለውና ስኬታማ የሆነ ንግድ እንዲጀምሩ ለመርዳት ነው። አብዛኛው ጊዜ እነዚህ የንግድ አርአያ የሚባሉት ከፍተኛ የሆነ የንግድ ልምድ ያላቸው ናቸው።

እነዚህ የንግድ አርአያ የሆኑት ሰዎች፣ በስምምነቱ መሰረት ሚስጢሩ የተጠበቀ ለተወሰነ ጊዜ የምክር አገልግሎት ያቀርባሉ፣ ይህ ጊዜ ደግሞ በተለምዶ ከስድስት ወር እስከ ዓመት ይደርሳል።

→ አንዳንድ ማህበሮች፣ የንግድ አርአያ ለመሆን የሚያጠቃልል የንግድ መጀመር ጥንቅር ያዘጋጃሉ። የነዚህ ጥንቅሮች ዝርዝር ማቅረብ አለብዎት።
→ አብዛኞቹ የንግድ አርአያ የሆኑ ሰዎች፣ የሚሰጡት አገልግሎት በበጎ ፍቃዳቸው (በነጻ) ስለሆነ ይህን አገልግሎት በተመለከተ አስቀድመው ማረጋገጥ አለብዎት።


© The Prince’s Trust and the Refugee Council 2006

ተጨማሪ መረጃ የት ለማግኘት ይችላሉ፡

**የንግድ መጀመር እርዳታ፤**

→ መመርያ 12 የእርዳታ ምንጮች፡ ንግድ ለመጀመር የሚተባበሩትን ማህበሮች ዝርዝር ስም ያቀርባል፡ www.refugeesintobusiness.org.uk/guide

**ለመረጡት ዓላማ የሚሆኑ አገልግሎቶች፤**

→ ዘ ፕሪንስስ ትራስት (The Prince's Trust) የሚባለው ማህበር የራሳቸው ንግድ ለመጀመር የሚፈልጉ ስራ የሌላቸው እድሜያቸው ከ 18 – 30 ለሆኑት ወጣቶች የሚረዳ ማህበር ነው። www.princes-trust.org.uk

→ Shell LiveWire የሚባለው ማህበር ደግሞ እድሜያቸው ከ 18 – 30 ለሆኑት ወጣቶች የራሳቸውን ንግድ ለመጀመርና ለማሳደግ የሚተባበር ማህበር ነው። www.shell-livewire.org

→ The Prime Initiative ይህ ብሔራዊ የሆነ ማህበር ደግሞ፡ እድሜያቸው ከ 50 ዓመት በላይ ለሆኑት ሰዎች የራሳቸውን ንግድ ለመጀመር የሚተባበር ነው። www.primeinitiative.org.uk

**ለሁሉም የሚሆኑ አገልግሎቶች፤**

→ በአከባቢው የሚገኝ ቢዝነዝ ሊንክ (Business Links) www.businesslink.gov.uk.

→ የአከባቢው የንግድ ወኪሎች (Local Enterprise Agencies) (LEAs) www.nfea.com

→ የአከባቢው የንግድ ምክር ቤት (Chamber of Commerce) www.britishchambers.org.uk

→ በቢዝነስ ላይ በፈቃደኝነት የነጻ ትምህርት ፕሮግራም (Business Volunteer Mentoring (BVM) Programme) www.bvm.org.uk

# ደርጃ 10: ሌሎች የእርዳታ ምንጮች

ቤተሰቦች፣ ጓደኞችና፣ ማህበረሰቦች የበለጡ የእርዳታ ምንጮች ናቸው። ምክንያቱም የእርስዎ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን በደንብ ስለሚያውቁት። ስለሆነ፣ ከነሱና ከነዚህ ባለሙያ የሆኑት አካሎች ምክር በማግኘት በመጨረሻ ላይ የሚጀምሩትን አዲስ ንግድ ለእርስዎ ይሆናል አይሆንም ለመወሰና ንግዱም በምን ዓይነት መልኩ ማካሄድ እንደሚችሉ እርዳታ ሊያገኑ ይችላሉ።

**ከአንጎላ የመጡት ማርያና ልዊሳ የሚባሉ ስደተኞች**

ማርያና ሊዊሳ ጓደኛሞች ናቸው። ሁሉቱም አንጎላውያን ሆነው በማንቸስተር በአንድ ሰፈር የሚኖሩ ናቸው። ማርያ ምግብ ቤት ለመክፈት ሃሳብ ስላላት፣ ምን ማድረግ እንዳለባት እየተወያዩበት ናቸው...

***ልዊሳ፣*** ይህ በጣም ጥሩ ሃሳብ ነው ማርያ! እንዲያውም ሁሌ የምትሰሪው ምግብ በጣም ቆንጆ ነው! በተጨማሪም ከሰዎች ጋር በቀላሉ የመግባባት ችሎታ አለሽ። እዚህ ሰፈር ደግሞ ምግብ ቤት በደንብ ሊሰራ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ጓደኞቻችን በተለይም ወጣት እናቶች የሚገናኙበት ቦታ ከትገኘ ጥሩ ሃሳብ ነው።

***ማርያ፣*** ነገር ግን ይህን ንግድ ለመጀመር ገንዘብ ከየት ለማግኘት እችላለሁ?

***ልዊሳ፣*** የአጎቴ ልጅ ጀምስ የራሱ ንግድ ስለጀመረ ሊተባበረን ይችላል።

***ማርያ፣*** በጣም ጥሩ ሃሳብ ነው። ወድያውኑ እጠይቀዋለሁ።

***ልዊሳ፣*** ሌላ ሃሳብም አለኝ ማርያ፤ ከሁለት ሳምንት በፊት ወደ ጓደኛየ ሱዛን ለእራት ግብጃ ሄጀ ነበር። በኦልድ ትራፎርድ የሚገኝ አፍሮ ካሪቢያን የሚባል በጣም ቆንጆ የሆነ ምግብ ቤት ነበር የሄድነው። የምግብ ቤቱ ባለቤት ደግሞ የሱዛን አጎትና አክስት ናቸው። ይህን ንግድ ከመጀመርሽ በፊት ለምን ምግብ ቤቱ ለጥቂት ሳምንቶች ያለክፍያ አትሰሪም፣ ይህ ደግሞ ስራው ላንቺ ይሆናል ወይም አይሆንም ለመወሰን ይረዳሻል። ከሱዛን ጋር ላገናኝሽ እችላለሁ።

***ማርያ፣*** በጣም ጥሩ ሃሳብ! እንድያውም የአንጎላ ምግብን እንድሰራ ከፈቀዱልኝ፣ ሰዎች ይወዱታል ወይም አይወዱትም ለማወቅ ይረዳኛል። ልዊሳ ስለ ሰጠሽን ሃሳብ በጣም ነው የማመሰግንሽ።


© The Prince's Trust and the Refugee Council 2006

ለጓደኞች፣ ቤተሰቦች ወይም ከአከባቢው ሰዎች ሃሳብዎን ማካፈል፣ ቀጥሎ ለተገለጹት ነገሮች ለማወቅ ያስችሎታል፤

- **ጠንካራ ጎንዎን ለማወቅ፣** ልዊሳ ማርያን በደንብ ታቃታለች። ስለሆነ የልዊሳ ሃሳብ፣ ማርያን ንግዱ ለመጀመር የሚፈለገውን ሙያ አላት ወይም የላትም ለይታ ለማወቅ አስቻላት።
- **የበጎ ስራ የሚሰራበት ዕድል ማግኘት፣** በዚህ ምግብ ቤት በመስራት ማርያ፣ ምግብ ቤት መክፈት ምን እንደሚያስፈጋት ለይታ ለማወቅ ሃሳብ ሊሰጣት ይችላል።
- **ሃሳብዎን ለመሞከር፣** ማርያ ከልዊሳ ጋር ንግዱን በተመለከተ ስለተወያየች፣ በሰፈሩ ምግብ ቤት እንደሚሰራ ለማወቅ አስቻላት።
- **ንግድን ለመጀመር ስላሉት እርዳታዎች የበለጠ መረጃ ማግኘት፣** ማርያ ጀምስን ምግብ ቤት እንዴት እንደከፈተውና ብድር ከየት እንዳገኘ ልትጠይቀው ትችላለች። ይህ ደግሞ ንግዱን ለመጀመር ትልቅ መረጃ ነው።
- **አርአያ/አማካሪ የሚሆንህ ለይቶ ማወቅ፣** ማርያ ጀምስን ወይም የሱዛን አክስት እና አጎት የራሳቸው ንግድ ስለ አቋቋሙ የንግድ አማካሪ እንዲሆንዋት ልትጠይቃቸው ትችላለች።

| ማድረግ ያለብዎት ነገር | ማድረግ የሌለቦት ነገር |
|---|---|
| ከጓደኞች፣ ቤተሰቦችና ከማህበረሰቡ ሊያገኙት የሚችሉትን ድጋፎች በሙሉ ይጻፉት። በተጨማሪም ንግድ ለመጀመር የሚተባበሩትን ማህበሮችን እርዳታና የንግድ አማካሪ እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይገባል። | ጓደኞች፣ ቤተሰቦችና ማህበረሰቡ ትክክለኛ የሆነ መረጃ ላይኖራቸው ስለሚችል፣ ሙሉ ለሙሉ ከነሱ ተስፋ ማድረግ አይገባም። ምክንያቱም ንግዱ ካልተሳካ ሃላፊነት የላቸውም። አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ የባለሙያ |

ይህ የመረጃ ጽሁፍ ለረፍዩጂ ካውንስል (Refugee Council) ተብሎ በ ፐሪንሰስ ትራስት (The Prince’s Trust) የተዘጋጀ ሆኖ እንዴት ለመጀመር እንደሚችሉ ማብራርያ ለማቅረብ ብቻ ነው። ስለሆነ በግልዎ ተጨማሪ የህግና የገንዘብ እርዳታ መፈለግ አለብዎት። ስለዚህ የዚህ ጽሁፍ አሳታሚ ማንኛንም ዓይነት ህጋዊ ሃላፊት የለውም። የረፍዩጂ ካውንስልና ፐሪንሰስ ትራስት ጽህፈት ቤቶች ደግሞ በዚህ ጽሁፍ ለተሰጡት መረጃዎች ትክክለኛነት አስመልክቶ ተጠያቂዎች አይሆኑም።

 © The Prince’s Trust and the Refugee Council 2006

rib

REFUGEES INTO BUSINESS

Cover design by Morse-Brown Design
© The Prince's Trust and the Refugee Council 2006